# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት

## የግንቦት ምእራፍ አልተዘጋም! አይዘጋም!!

የግንቦትን የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ ድሎች የማስከበሩ ጉዳይ የዚህ ወይም የዚያ ድርጅት፤ የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ ጉዳይ ሳይሆን በጠቅላላው በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና በእያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት ትከሻ ላይ የሚወድቅ ታሪካው ተልእኮ ነው። በዚህ ታሪካዊ ተጋድሎ እኛ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ስር ተደራጅተን የምንዋደቅ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶች ህብረታችን "ዜጎች ለግንቦት ድሎች ይሰባሰቡ" በሚል ያቀረበውን አገራዊ ጥሪ ለፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ተቀብለው በያሉበት የህዝባችንን ድል ለማስከበር ዘብ መቆማቸውን ተመልክተን በዚች አገርና በህዝባችን ያለንን እምነት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ እንዲጎለብት አድርጎታል።

ሆኖም እንደኛው ለዚች አገራችን ዘብ እንድትቆሙ ጥሪ ያደረግንላችሁ ወገኖቻችን ከቅርብ ሳምንታት ወዲህ በተፈጠሩ ውዥንብሮች የተነሳ ትግሉ በማሳየት ላይ ባለው የመንገዳገድ ሁኔታ ከፍተኛ ጭንቀት ላይ እንደምትገኙ ከየአቅጣጫው የሚደርሱን ጥቆማዎች እያመለከቱን ነው። በኛ ግምት ዛሬ የምንገኝበት አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ያደረሱን ድክመቶች ባስቸኳዋይ ታርመው ለዚህ ተጋድሏችን አዲስ እስትንፋስ የመስጠቱን ጉዳይ የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገን ስለምንወስደው ስለ ቀጣዩ ትግል የሚታየንን አቅጣጫ ለወገኖቻችን ለማካፈል እንወዳለን። ዋናው መልእክታችን ግን ከወዲሁ ግልፅ ነው። የግንቦት ምእራፍ አልተዘጋም። አይዘጋምም።

ባለፉት ስድስት ወራት ህዝባችን የተነጠቁትን ታሪካዊ ድሎች መልሶ እጁ ለማስገባት ያካሄዳው ትግል ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሞታል። ብዙ መስዋእትነት ተከፍሎበታል። ሆኖም የተከፈለውን መስዋእትነት በሚመጥንና "ድል አይቀሬ ነው" ብለን አፍ ሞልተን ለመናገር በሚያስችል መልክ ትግላችን ስር እንዲሰድ፤ እንዲሰፋና እንዲቀነባበር ካላደረግን የግንቦት ድሎች እንደተነጠቁ ቀርተው ሃገራችንና ህዝባችን አንቅረው ወደ ተፉት አስከፊ ስርአት ተመልሰው የሚዘፈቁበት አደገኛ ሁኔታ ከፊታችን ተደቅኑዋል። ይህ ውድቀት ከመጣ የሚያስከትለውን ውጤት የኢህአዴግ መሪዎችን እብሪትና ፀረ ህዝብነት የሚያውቅ ማንም ዜጋ የሚስተው አይመስለንም። በያለበት ከአዲስ አበባ አንስቶ በየክልሉ በመቶ ሽህ የሚቆጠሩ ታጋይ ዜጎች ከኢህአዴግ ካድሬዎችና ከመንግስት ባለስልጣናት እየተፋጠጡና እየተጋፈጡ ገና ያልበረደላቸውን እብሪት እየተቋቋሙ ያቀጣጠሉት ትግል ሽንፈት ቢያጋጥመው እነዚህ ዜጎቻችን ለአስከፊ የአፈና ውርጅብኝ እንደሚጋለጡ ማንም ሊጠረጥር አይችልም።

በዚህ መልክ እነዚህ በትግላቸው ገፍተው ድል ከማድረግ ሌላ ምንም አማራጭ የሌላቸው ግንባር ቀደም ዜጎቻችን በሚጠይቁት መሰረት የዚህን ታሪካዊ ተጋድሎ አመራር ወደንና ፈቅደን የተቀበልን ወገኖች በአንድ በኩል ለትግሉ ጥራትና አቅጣጫ እየሰጠን ታግለን የማታገል በሌላ በኩል ደግሞ በያለበት በትግሉ ካገኙት ተመክሮ እየታገዙና በያለበት የህዝባችንን የልብ ትርታ እያዳመጡ የምያቀርቡዋቸውን ሃሳቦች እኛም የማዳመጥ ግዴታ እንዳለብን እንገነዘባለን። በመሆኑም በያለበት ላላችሁ ታጋይ ዜጎች ህብረታችን ዛሬ እየተከሰተ ካለው ሃላፊና ጠፊ ውዥንብር ባሻገር የተያያዛችሁት የግንቦትን ድሎች የማስከበር ተጋድሎ እየሰፋ፤ እየተቀነባበረና እያየለ ሄዶ ለአይቀሬው ህዝባዊ ድል እንዲበቃ ከድርሻችን በላይም ቢሆን አስተዋፅኦ ለማድረግና ከእናንተና ከህዝባችን ጋር ለድል ለመብቃት ያለንን ቁርጠኛነት እናረጋግጥላችኋለን። ለዚህ ደግሞ በሚቀጥሉት ቀናትና ሳምንታት መከተል ስለሚኖርብን የትግል አቅጣጫ ያለንን ሃሳብ ከመሰንዘራችን በፊት የተወሰኑ የህብረቱ አባል ድርጅቶች የብዙሃኑን ውሳኔ ጥሰው በኢህአዴግ ፓርላማ በመግባታቸው ሳቢያ ስለተፈጠረው ቀውስ ያለንን አስተሳሰብ ለማካፈል እንፈልጋለን።

ፓርላማ መግባት የለብንም የሚለው ውሳኔ የጥቂት ድርጅቶች አመራሮች ብቻ የወሰኑት ውሳኔ አይደለም። የህብረቱ ተወዳዳሪዎች ከሶስት ወራት በፊት ከመላ ሃገሪቱ ተጠራርተው በአዲስ አበባ ባደረጉት ጉባኤ፤ ከዚያም

ለመስከረም 20 እና 21 ታስቦ ለነበረው ስብሰባ አዲስ አበባ ተገኝተው የነበሩት ታጋዮች በአመዛኙ ያንፀባረቁት ህዝባዊና ትክክለኛ አቋም ነው። ይህ ተቃውሞ የሚመነጨው በፓርላማው መከፈት ቀን ጀምሮ የተንፀባረቀውን የተሳትፎ ፋይዳ ቢስነት በማጤን ብቻ ሳይሆን ተሳትፎ የሚያስከትላቸውን መዘዞች በመፍራትም ነበር። ዛሬ እነዚህ መዘዞች አፍጠውና አግጠው ተከስተዋል። ሆኖም በትግላችን ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ችግሮች በብስለትና በቆራጥነት መዋጋት ይኖርብናል። ይህ ደግሞ አንድ ነገር ብቻ ማለት ነው። ሰባ ሰባት ሚልዮን ህዝብ ከጀርባው አሰልፎ በመቶ ሸህ የሚቆጠሩ ዜጎች ሃብታቸውን፤ ጉልበታቸውን፤ መፃኢ እድላቸውንና አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ ህይወታቸውን እየለገሱ በማካሄድ ላይ ያሉት ግንቦት የወለደው ታሪካዊ ተጋድሎ ሃምሳም ሆነ መት ወይም መቶ ሃምሳ ሌሎች ዜጎች እዚህ ህገ ወጥ ፓርላማ በመግባታቸው ምክንያት ምንም አይነት አሉታዊ ጫና እንዳይኖረው እየተጠነቀቅን ወደፊት ጉዞዎችንን መቀጠል አለብን፤ እንቀጥላለን ማለት ብቻ ነው።

ከዚህ በመነሳት የህብረቱን ውሳኔ ጥሰው ፓርላማ በገቡና በቀሩት ታጋዮች መሃከል ኢህአዴግ እንደሚመኘው የሰፋ ክፍፍል እንዳይኖር ሁሉም ወገኖች በከፍተኛ ጥንቃቄ የመራመድ ግዴታና ሃላፊነት እንደሚኖርባቸው ተገንዝቦ መንቀሳቀስ ብቻ አይደለም። ከዚህም አልፈን በዚህ በተወሰኑ ዜጎች በተወሰደ እርምጃ የኢህአዴግ መሪዎች በፕሮፓጋንዳው፤ በፖለቲካውና በዲፕሎማሲው መስክ ሊቃርሙ የሚቃጣቸውን ጥቅም ጥራት ባለው ዘዴ ትግላችንን አፋፍመን ልንቁዋቁዋመው ይገባል ማለት ነው።

የኢህአዴግ መሪዎች በተወሰኑ ዜጎች ፓርላሜንት ውስጥ መግባት ሳቢያ የግንቦቱ ምርጫ ፋይል ተዘግቷል ሊሉን ይቃጣቸዋል። እኛ ደግሞ ህዝባችንን ከዳር እስከዳር በማሰለፍ ለግንቦት ድሎች የሚካሄደው ተጋድሎ ገና የሚቀጥልና የሚፋፋም መሆኑን ልናረጋግጥላቸው ይገባል። የኢህአዴግ መሪዎች ከፓርላማ ውጭ የሚካሄደውን ትግል "ህገ ወጥ" አርገው በአመፅ ለመደምሰስ ላይ ታች ሊሉ ይችላሉ። እኛ ደግሞ ሌላው ቀርቶ ከራሱ ከኢህአዴግ ህገ መንግስት አንፃር ህገ ወጡ ይህ የድምፅ ሌቦች ዋሻ የሆነው ፓርላማ መሆኑን ለማሳየት ያላሰለሰ ትግል ማካሄድ ይኖርብናል። የኢህአዴግ መሪዎች ቀጣዩንና አይቀሬውን ትግል የጥቂቶች ሴራና አጉል መፍጨርጨር አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። እኛ ደግሞ "ጥቂቶቹ" እነሱ እንጂ የኛ ተጋድሎ አንድ ህዝብ በነቂስ አሻፈረኝ ብሎ የሚንቀሳቀስበት ማእበል መሆኑን በተግባር ማሳየት ይጠበቅብናል። አለም አቀፍ ኮሙኒቲ የተባለውም ራሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ ካለው ህልም የማይመጥንና አለም አቀፍ የምርጫ መስፈርቶችን አያሟላም ብሎ ያጣጣለውን ሂደት እዛው በዛው በአንድ ራስ ሁለት ምላስ በመሆን "ለናንተ ያህል ይበቃል" በሚል ንቀት የተወሰኑ ዜጎች ፓርላማ በመግባታቸው ብቻ ህዝቡም ውጤቱን እንዲቀበል አንዳንድ ግፊት እያደረገ መሆኑን እናውቃለን። ይህንን ግፊት ከሃገራችን ካለፈ ታሪክ፤ ዛሬ ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታና ለነገይቱ ኢትዮጵያችን ካለን ህልም እየተነሳን የሰላማዊ ትግል ስትራቴጂ የመቀየሱን ሃላፊነት ለኛ ለሃገሪቱ ታጋይ ሃይሎች እንዲተውትና እነሱ ለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያን ራሳችን ለራሳችን ለምናደርገው ሰላማዊና ህጋዊ የዴሞክራሲ ትግል በአጋዥነት ብቻ እንዲሰለፉ ለማሳሰብና ታጋይ ህዝባችን በዴሞክራሲ ፍርፋሪ እንደማይረካ ለማሳየት ከዳር እስከዳር "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" ብለን በአንድ ልብና በአዲስ ወኔ መነሳት ይኖርብናል።

ይህንን ስንል አሁንም አላማችን ምን እንደሆነ በግልፅ እናስቀምጣለን። የኛም ሆነ የጠቅላላው የህብረተሰባችን የትግል አላማ በግንቦት 97 በህዝብ ደምና መስዋእትነት ተገኝተው የነበሩትንና ዛሬ በኢህአዴግ በመነጠቅ ላይ ያሉትን ድሎች የማስመለስን ያህል ክቡር የሆነ አገራዊ አላማ ነው። ለዚህ ደግሞ አንድ ሽ አንድ ትርጉም የለውም። የህዝባችን ድምፅ ተከብሮ የግንቦትን የሰላም፤ የዴሞክራሲና የብሄራዊ እርቅ ድሎች ለማጎልበት ሁኔታዎች እንዲመቻቹ እንዋደቅ ማለት ነው። የትግሉ ስልትም ለኛ ከፀሃይ በደራ ሁኔታ ግልፅ ነው። ህዝባችን መዋደቁና መስዋቱ ሳይቀር አሁን እንደሚታየው በያለበትና ተራ በተራ እየተነሳ በያለበትና ተራ በተራ እየተመታ ወደ አስከፊ ውድቀት እንዳይነጉድ በአገር አቀፍ ደረጃ ሁሉም እጅ ለእጅ ተያይዞ እንዲራመድ እንጥራለን።

ከዚህ አንፃር ሲታይ ባለፉት ጥቂት ሳምንታት በአንድ በኩል ለትግሉ ቀጣይነትና ቅንብር ሲባል የሚወሰኑ እንደ አገር አቀፍ የታጋዮች ጉባኤ አይነት የትግል ቀጠሮዎች ተፈፃሚነት በማጣታቸው በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ትግል ውስጥ ወሳኝ የሆነውን ህዝባዊ ተሳትፎ ለማረጋገጥ የተነደፉ እቅዶች ለህዝቡና ለታጋዮች በሚሰጡ የጥሪ

ዥዋዥዌዎች ምክንያት *ተግባራዊ ባለመሆናቸው* ህብረተሰባችን ለቅልበሳ *በሚመች* አደገኛ ውዥንብር ውስጥ እንዲወድቅ ተደርጓል። ከዚህ ችግር ወጥተን ወደ ድል የሚመራንን አቅጣጫ ለመያዝ በመነጠቅ ላይ ያሉት የግንቦት ድሎች መልሶ ወደ ህዝባችን እጅ ለማስገባት የሚደረገው ትግል ያገባናል የሚሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የሲቪኩ ማህበረሰብ ድርጅቶች ማህበራትና መሪዎች እንዲሁም በአጠቃላይ ዴሞክራሲያዊ ዜጎች *በአስቸኳዋይ በሶስት ቁም* ነገሮች ተስማምተው መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል።

አንደኛ በሚቀጥሉት ቀናት ዜጎች ሁሉ እንደ አን-ድ ሰው ሆነው በአንድ ድምፅ የሚንቀሳቀሱበት የጋራ ግልፅ አጀንዳ ስለማስፈለጉ፤

*ይ-ህ የጋራ አጀንዳ የመጠቆሙ ጉዳይ በቅ-ድሚያ በትግሉ መስክ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ በመሆኑ አሁን በሁለቱ ዋና ዋና ተቃዋሚ ድርጅቶች ማለትም በህብረቱና በቅንጅቱ መሃከል በዚህ ጉዳይ የሚንፀባረቁት ፁጭብጥም ባይሆን የትኩረት ልዩነቶች ተጣጥመው አንድ የጋራ የትግል አጀንዳ መልክ የሚይዙበት ሁኔታ መመቻቸት ይኖርበታል።*

ህዝባችን ለታጋይ መሪዎቹ የሰጠው አደራና ተልእኮ በምንም በማያሻማ ሁኔታ ግልፅ ነው። የተሰረቀ ድሌን ለማስመለስ በማደርገው ትግል አመራር ስጡኝ የሚል ጥሪ ነው። ህብረታችን ለዚህ የህዝብ ጥሪ መልስ በመስጠት ባለፈው መስከረም ....ቀን " ዜጎች ለግ-ንቦት ድሎች ብለን እንሰባሰብ " በሚል ርእስ ባወጣው መግለጫ የት-ኩረት ትኩረት የሚሰጠው ለዚህ አላማ መሆኑን በማስረገጥ በሰባት ነጥቦች ዙሪያ እን-ቅስቃሴ እንዲደረግ ጥሪ አድርጉዋል። የቅንጅት ወገኖቻችን በበኩላቸው የድርጅቱ ተመራጮቹ ፓርላማ እንዲገቡ ከተፈለገ መሟላት አለባቸው የሚሏቸውን ስምንት ቅድመ ሁኔታዎች *አስቀምጠው* ኢህአዴግ ተደራድሮ እነዚህን ነጥቦች እንዲያሟላ ጥሪ አድርገዋል። ለትግሉ ጥራትና አንድነት ሲባል ይህ ክፍተት ባስቸኩዋይ ተደፍኖ ከስምንቱ የቅንጅ-ት ነጥቦችና ከሰባቱ የህብረቱ ነጥቦች ተውጣጥቶም ቢሆን *ነገር ግን ደግሞ* ለህ-ዝቡ ድል መከበር ቅድሚያ በሚሰጥ ሁኔታ አንድ የጋራ አጀንዳ እንዲነደፍ ደጋፊዎቻችንና አባሎቻችን ከነሱም ባሻገር የግንቦት ድል ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ሁሉ አን-ድነታቸውን አጠንክረው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ እናስተላልፋለን።

ሁለተኛ በሚቀጥሉት ቀናት ከድርድር ይልቅ ለህ-ዝባዊ ትግል ትኩረት ሰጥተን በጋራ መንቀሳቀስ ስለማስፈለጉ፤

ህዝባችንን ሳንይዝ ባእዳን ሃያላን በርቱ ግፉ ስላሉን ብቻ ከኢህአዴግ ጋር የሚሞከረው ማንኛውም ድርድር የትም እንደማያደርስ ሌላው ቢቀር የቤት መዋሉን አድማ ለማሰረዝ ብቻ ኢህአዴግ *የቃጣውንና* ይህንን ተልእኮውን *ከፈፀመ በኋላ ወዲያውኑ የተቋረጠውን* ድርድር ተብየ ትያትር *ማስታወስ ብቻ ይበቃል።* በሁለተኛው የህብረታችን ጉባኤ በትክክል እንዳስቀመጥነው ከእንግዲህ በህዝብ ትግል ያልታጀበ ድርድር የትም እንደማያደርስ ስለምንረዳ በዚህም ጉዳይ ተቃዋሚ ሃይሎች አንድ የጋራ አካሄድ መንደፍ ይኖርባቸዋል። በህብረቱ በኩል ህዝባችን ካልገባበት በድርድር ምንም አይገኝም ብቻ ሳይሆን በአደራዳሪዎች *ግፊት የህዝቡ ድምፅ* ይከበር ከሚለው አላማችን አንፃር እዚህ ግቡ የማይባሉ *አንዳንድ* ድሎች ከኢህአዴግ እጅ ቢፈለቀቁም እንኩዋን ለተፈፃሚነታቸው ምንም ዋስትና *ሊኖር አይችልም የሚል ፅኑ እምነት እንዳለ ለማስረገጥ እንወዳለን።* በመሆኑም የጋራ እንቅስቃሴ ስንል በውጭም በውስጥም ዜጎች ከዳር እስከዳር የግንቦት ድሎችን መከበር ጉዳይ በግንባር ቀደምነት አንስተው በቤት መዋልና በሌሎች ሰላማዊ የትግል ስልቶች *በመጠቀም በቅድሚያ ህዝባችንን የትግላቸው ዋና ተዋናይ እንዲያደርጉና የኢህአዴግ መሪዎችን ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጡ እናስገድዳቸው ማለት ስለሆነ* አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችንና ከነሱም አልፎ የግንቦት ድሎች መከበር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ሃይሎች ሁሉ አንድነታቸውን አጠንክረው *"ከድርድር ህዝባዊ ትግል ይቅደም" ብለው* እንዲነሳሱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ሶስተኛ ለጋራ ትግላችን አገር አቀፍ መሰረትና ቅንብር ለማጎናፀፍ አስቸኳዋይ አገር አቀፍ የታጋዮች ጉባኤ ስለመጥራት

ህብረቱና ቅንጅቱ የጠሩትና ለትግሉ አዲስ እም-ርታ ማግኘትና ለአገር አቀፍ ቅንብሩ ወሳኝ ነው ብለን *የገምተነውና ለመስከረም 20 እና 21* ታስቦ የነበረው በያለበት የሚዋደቁ ታጋይ ዜጎችን የሚያካትት አገር አቀፍ ጉባኤ አዳራሽ አልተገኘም ተብሎ እንዲሰረዝ ተደርጉዋል። ስለዴሞክራሲና ስለ ዜጎች ህገ መንግስታዊ መብቶች ሌት ተቀን የሚያቅራሩት የኢህአዴግ መሪዎች *በአዳራሽ የመሰብሰብን* ያህል እዛው በዛው መሰረታዊም ቀላልም የሆነ መብት እስከ ማገድ ቢሄዱና በዚህም ቢያንስ በአሳዳሪዎቻቸው ፊት መጋለጥን ቢመርጡ ለዚህ ሊኖር የሚችለው አንድ ምክንያት ብቻ ነው። ትግሉ ከጥቂት መሪዎች ሰፍቶ በመላ በሃገሪቱ በመዋደቅ ላይ ባሉ ዜጎች በተነደፈ ስትራቴጂ መመራቱ፤ ትግሉ አንዱ ለሌላው ጀርባውን ሰጥቶ ሁሉም በየፊናው የሚያካሂደው መሆኑ ቀርቶ በአገር አቀፍ ደረጃ የተቀነባበረ መሆኑ ለነሱ የሞት ሽረት ጥያቄ መስሎ ስለታያቸው ነው። እኛም ነገ ሽንፈት ቢመጣ የአስከፊ አፈናውን ገፈት የሚጋፈጡትን ታጋይ ዜጎች ሰብስበን ከህዝብ የልብ ትርታና ከትግል ተመክሩዋቸው የሚፈልቅ አገር አቀፍ ስትራቴጂ የማውጣቱን ጉዳይ እንደ ኢህአዴግ መሪዎች የሞት ሽረት ጥያቄ አድርገን መውሰድ ይኖርብናል። በመሆኑም ይህንን አገር አቀፍ ጉባኤ እንደገና መጥራትና አሁን ግን ቁርጠኝነቱ ኖሮ ኢህአዴግ የአዳራሽ ስብሰባ እስከመከልከል ዘልቆ የዜግነት መብታችንን ከነፈገን ካስፈለገ ድንኩዋን ተክለን ይህ ባይቻል ደግሞ ሜዳ ላይ ተሰብስበን እዛው በዛው ጉባኤውን ማካሄድና ለመላው አለም የኢህአዴግ ዴሞክራሲ የአዳራሽ ጉባኤን እንኩዋን የማይፈቅድ የወስላቶች ልፈፋ መሆኑን ማጋለጥ ይቻላል ብለን ስለምናምን አባሎቻችን፤ ደጋፊዎቻችንና ከነሱም ባሻገር የግንቦት ድል ያገባናል የሚሉ ዜጎች ለዚህ ጉባኤ እውንነት እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ እናስተላልፋለን።

ዜጎች ለግንቦት ድሎች ብለን እንሰባሰብ!
የህዝብ ድል በህዝብ ትግል ይከበራል!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት
ጥቅምት 17 ቀን 1998 ዓ.ም.